ዘመኑ እስኪጣበብ ድረስ ሰአቲቱ አትቆምም።

ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል፦ "ዘመኑ እስኪጣበብ ድረስ ሰአቲቱ አትቆምም። አመቱ እንደ ወር ይሆናል፤
ወሩ እንደ ሳምንት ይሆናል፤ ሳምንቱም እንደ ቀን ይሆናል፤ ቀኑም እንደ ሰአት ይሆናል፣ ሰአቱም የተምር ዛፍ (ዘንባባ) ቅጠል እንደሚቃጠልበት ጊዜ (ያጠረ) ይሆናል።"
[ሶሒሕ ነው።] [አሕመድ ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ከሰአቲቱ ምልክቶች መካከል አንዱ የጊዜ መቀራረብ መሆኑን ተናገሩ። ዓመቱ ልክ እንደ ወር ያልፋል፤ ወሩም ልክ እንደ ሳምንት ያልፋል፤ ሳምንቱም ልክ እንደ ቀን ያልፋል፤ ቀኑም ልክ አንድ ሰዓት እንደሚያልፈው ያልፋል፤ ሰአቱም የተምር ዛፍ (ዘንባባ) ቅጠሉ በሚቃጠልበት ሀይለኛ ፍጥነት ልክ ቶሎ ያልፋል።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/65027